Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር Ref. No ፉ/ሒ/፫/5/18
ቀን Date 05 ጳጉሜ 2005

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

ባለልዩ መብት ድርጅቶች ለስራቸው ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ከአገር ውስጥ ሲገዙ ከጅምሩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ማድረግ የሚያስከትለውን የአፈፃፀም ችግር ለማስወገድ በተመላሽ ታክስ እንዲስተናገዱ የሚያስችል መመሪያ መ/ቤታችን አውጥቶ እየተሰራበት መሆኑን እንዲሁም በሰብአዊ እርዳታ መልክ የሚቀርቡ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ከጅምሩ ከታክሱ ነፃ ማድረግ ተመሳሳይ ችግር ስለሚያስከትል በሰብአዊ እርዳታ መልክ ለሚቀርቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶችም ጭምር የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አሠራር ተፈፃሚ እንደሚሆን የሚያሳውቅ መመሪያ ማውጣታችሁን አስታወሳችሁ ሰብአዊ እርዳታ የሚያቀርቡ ድርጅቶች ከጅምሩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ከመ/ቤታችን በሚፃፍ ደብዳቤ የሚሰጥ ፈቃድ በተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መብት አፈፃፀም አንድ ወጥ አሠራርን በመከተል ረገድ ችግር ያስከተለ በመሆኑ በመ/ቤታችን የሚሰጠው ከጅምሩ ከታክሱ ነፃ የመሆን ፈቃድ በሥራ ላይ ካለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ (Refund) አሠራር ጋር ተገናዝቦ መፍትሔ እንዲሰጥ በ21/12/2005 ዓ.ም በቁጥር 6.1.0/1781/61 በተፃፈ ደብዳቤ የጠየቃችሁትን ይመለከታል፡፡

የተመላሽ ታክስ ሥርዓት ከታክስ ነፃ የመሆን መብት አፈፃፀም ስልት ወይም ሞዳሊቲ ነው፡፡ ስለሆነም ከመ/ቤታችን በሚፃፍ ደብዳቤ ለሰብዓዊ ዕርዳታ አላማ በአገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ግዥዎች ጋር በተያያዘ የሚሰጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መብት ፈቃድ ተፈፃሚ መሆን ያለበት በመመሪያው መሠረት በታክስ ተመላሽ ስርዓት ነው፡፡ ነገር ግን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት የሚደርስ ጉዳትን ለመቋቋም መንግስት ባስተላለፈው ጥሪ መሠረት ለሚቀርብ አስቸኳይ የምግብና ሌላ አስፈላጊ እርዳታ የሚፈፀም የሀገር ውስጥ ግዥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መብት አፈፃፀም በታክስ ተመላሽ ስርዓት እንዲመራ ማድረግ ተገቢ ባለመሆኑ መመሪያው የዚህ ዓይነቱ መብት በልዩ ሁኔታ እንዲስተናገድ ይፈቅዳል፡፡

ስለዚህ በተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት የሚደርስ ጉዳትን ለመቋቋም መንግስት ባስተላለፈው ጥሪ መሠረት ከሚቀርብ አስቸኳይ እርዳታ በስተቀር የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት የአገር ውስጥ ግዥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መብት በተመላሽ ታክስ አሠራር መሠረት ተፈፃሚ መሆን እንዳለበት እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

Letter/B/ET

ስልክ TEL 251-11-155 24 00, 22 66 98
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905, 1037
ፋክስ FAX. 251-11-155 13 55, 55 14 96 251-11-155 38 44
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵ Addis Ababa - Ethi